# ሞትና ቅዳሴ፡ ነፍስና ውዳሴ

ነብስ’ና ውዳሴ...
ሰመአት ሆንክና፣
ላስብህ ተነሳሁ...
በትዝታህ ግርሻ...
ውስጤን እያሳሳሁ...
ትናንትን ተርፌ፣
አንተ ለኔ ሞተህ፣
ካንተ ሞት ዘለላ...አንጉዋን አስተርፌ ...
ሞትህን ተጽፌ....
ማህሌት ቆምኩልህ፣
በንባ ጽናጽል፣
አንተ የኔ አላፊ፣
እኔ ያንተ ቅጽል ....
ትዝ ትለኛለህ፣
የነበረህ ስሜት፣
ከበራሪው ጥይት ...
ልብህ ውስጥ ያደረው፣
ይጠበቀው እውነት ...
ትዝ ትለኛለህ ....
ዛሬ አንተ የለህም፣
አንት ሙዋች መስዕዋት...
እኔ ደሞ ቆዋ’ሚ፣
ልክህን ገጣሚ፣
ለሞትህ ሰዳሪ፣
የቅኔ ዘራፊ፣

አንጉ-ዋና ምቼትን፣
ለፈሰሰው ደምህ፣
ለነብስህ ጠላፊ ...
ለ-ሞትክ ዘራፊ ...
ይኸው ጊዜ ክፉው...
እኔ ቁዋ’ሚ ሆኜ፣
አንተን አበው አር’ጎ
ያሳለፍነው ነገር ከደም ስሬ ሰርጎ...
እምባዬ እየመጣ፣
እልኼ እየምጣ ...
መሓል ላይ ትዝታህ ተንጠ እየወጣ...
ከግጥምም ግጥም፣
ሞትህን ገጠምኩት...
የቁዋሚ ሙዋ’ች ሆኜ፣
ትዝታህን ኖርኩት ...
የዘጽአት ልጆች... ነጻነትን ብለን፣

በንጹህ ልቦና ናፍቀን አዲስ ዘመን፣
ከ-ን-ዐን ልንገባ አ-ስ-ኩ-ዋ-ላውን ከበን...
መዝሙር ስናሰማ....

ደምና ጉዋጉንቸር፣  ቅማል እና አንበጣ፣
ፍቅራችን ነበረ ጠላትን የቀጣ...
የ-ዘ-ጸ-አ-ት ልጆች ነጣነትን ያልን፣
ኮ-ሮጆው ተቀዶ በደም የታጠብን...
ለዚያች ጥቁር አፈር ልጆቹዋ ነብርን...
ልጆቹዋ ነበርን...
ተስፋን የሰነቅን፣
በቀን በጠራራ፣
በጥይት ያለቅን...

ልጆች-ዋ ነበርን፣
ዘራችን ተቆጥሮ፣
እግርና እጃችን ፍጢኝ ተጠፍሮ፣
በየመታጎሪያው የተወረወርን፣
ልጆችዋ ነበርን፣
እየተረገጥን ሜዳ ላይ ያደርን።
አሻጋሪው ነብይ፣
ህዝቦቹን ረስቶ፣
ለበርሬቹማ ጥጃ፣ ባድዋ-ዎች ኮሬብ ጽናቱ ተፈቶ፣
ሊያውም ትናንትና፣
በዚያ በጠራራ፣
የፈሰሰው ደምህ ካፈሩ ሳይጠራ፣
የሞትክ ትዝታ ገና ሳያባራ፣
ክምርጫ ዘመቻ ተ-ርቅ አደባባይ፣
ድንኩ-ዋኑን ሲተክል፣ ተ-መቃብርህ ላይ፣
እሱን ተከትለህ መሞትህን ሳስብ...
አጥንቴን ቢበላኝ፣
ልቤ ውስጡ ቢላብ...
ትዝታህን ብራብ፣
አንተ አፈር ሆነህ....
ቀየው ላጭበርባሪ፣ ሲሆን ለደላላ....
"እውነትም ሀገሬ የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ!".....
ከማለት በስተቀር ሌላ ምን እላለሁ....

እንጂማ ለግዜ ዘመን ለመቁጠሪያ፣
ዘመንን ለመጥሪያ...
ማሰብ ሆኖን ስራ፣
መቶ አመት አልፈን ባድዋ ስንኮራ....
አሁን ምን ዋጋ አለው ትዝታህን ባስብ፣
ገጽታህን ብራብ...

እንክ-ዋንና አንተ-
በግ እንክ-ዋን ለኔ አልፉዋል፣
የኔን ሆድ ለመሙላት...
እኔ ግን ባዶ ነኝ፣ ያለተፈጠረብኝ የሚቆርጥ አንዠት፣
በብዙ መስዕዋት ቆሜ የምሄድ ከብት....

ከበጎቹ መኀል ጠፍቼ ያልተገኘሁ፣
በ-ዝክር ያድዋን ቅኔ የተቀኘሁ....
ከፍርሃት ዋሻ
ከክህደት ጢሻ
ጭራዬን ስቆላ እንደ ሶሎግ ውሻ....
ሙ-ሰዋት ያቃተኝ....
እኔ ነኝ ኑቢያ፣ እኔ ነኝ ሓበሻ!
ወገኔ ሲደማ፣
ስሙንና ክብሩን፣
መሬቱን ሲቀማ፣
ከቀዬው ሲገፋ፣
አንገቱን ሲደፋ....
እኔ ግን በሩቁ ስምህን ወርሼ፣
ክብርህን አርክሼ፣
አለሁኝ እያልኩህ...
እኔ ያንተ አሳቢ የተስካርህ ደራሽ፣
ለትዝታህ ዕልፍኝ፤ ተከራይ አዳራሽ...
አንተ ለኔ ፈራሽ....
ይህን ህይወት ብዬ፣ መሞትን ፈርቼ፣
አጨበጭባለሁ አዳራሽ ዘግቼ::

እናም ዛሬ ርቄ፣
አንተን ለመዘከር ግጥም ተጠይቄ...
ሊያውም ለወንድሜ፣
አብረን ለተራብነው
ካ-ውሬ የተረፈ አካል ለቀበርነው...
ምን ያረጋል ግጥም...
አፈር ላ-ያነሳ...
መሆንን ያቃተው: በስራህ ሊነሳ...
ምን ያደርጋል ቅኔ!
ምን ያደርጋል ወሬ!
እኔ አንተን ቀብሬ!
ታገር ተባርሬ!
ትዝታን ድንብሬ!
ምን ያረጋል ግጥም!
ምን ያ-ረጋል ወሬ?....
ግጥምስ መጋጠም...
ነበረ መፋጠም....
እሱ ነው መዘከር፣

**እሱ ነው መፈክር፣**
**መመለሻ-ያንተን ደም::**
**ወሬ ምን ያረጋል፣**
**ርቀው ቢያስቡህ ... ተመቃብርህ ላይ፣ ትልቅ ሙጃ ያድጋል....**

**ማስብስ እሱን ነው: ሊማ-ሊሞን መውረድ**
**እንዲህ ተበሻቅጦ ቁሞ ከመዋረድ....::**
**ሞትህን ከማሰብ: ምናለ ትግልህን ፋናህን ብከተል...**
**አድዋ ላይ ቁንጽል: ጭራ ከምቀጥል.....**
**ምናለ-ብከተል?!**
**መቼ ይሆን ዘካሪ: ተ-ዘካሪ ሆኖ....**
**የሚኖረው ሞቶ: በመሞቱ ገኖ!**

**መች ይሆን?**

**ከሂኖክ የሽጥላ....**